# የአንበሳ ግቢ ማስታወቂያዎች?

በአጼ ሃ/ሥላሴ ዘመነ መንግስት በ 6 ኪሎ አንበሳ ግቢ ውስጥ
የተለጠፈው ማስታወቂያ

<u>እባካችሁ ጎብኝዎቻችን</u>

የአንበሶቹ ምግብ በጥናት የሚዘጋጅ በመሆኑ ከውጭ ምግብ
እምጥታችሁ እንዳትመገቡዋቸው እንጠይቃለን!
የዘውድ አርማችን ናቸውና እናከብራቸው
የሚል ነበር አሉ።

ይህው ማሳሰቢያ በደርግ ዘመን ተለውጦ

<u>ጥብቅ ማስጠንቀቂያ</u>

አንበሶቹ የህዝብ ንብረት ናቸው።
በመሆኑም ምግባቸውን የበላ ጎብኚ ከጸራ አብዮተኛ ተነጥሎ
ስለማይታይ! አብዮታዊ እርምጃ ይፈጸምበታል!!
ግዚያዊ ወታደራዊ መንግስት። የሚል ሆነ

በዘመነ ወያኔ ደግሞ

<u>የጨረታ ማስታወቂያ</u>

መንግስት የግል ባለሃብቶችን ለማበረታታት እያደረገ ባለው ጥረትና የህዝብ
ድርጅቶችን ለጨረታ አቅርቦ የመሸጥ እንቅስቃሴ መሰረት
እነኚህን አንበሶች በቅርቡ በጨረታ ለመሸጥ ይፈልጋል፤።
አንበሶቹን የግል ሃብት ለማድረግ የምትፈልጉ ባለሃብቶች በጨረታው
መወዳደር የምትችሉ መሆኑን እናስታውቃለን።